## የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኤጀንሲ

## Ethiopian Telecommunication Agency

# ከውጪ ወደ ኢትዮጵያ የሚመጡ ተጓዦች ወደ ሀገር ውስጥ ማስገባት የሚችሉትን የቴሌኮሙኒኬሽን መሣሪያዎች እና ማሟላት ያለባቸው መረጃዎች በተመለከተ የተዘጋጀ መረጃ*

ኤጀንሲው በቴሌኮሙኒኬሽን አዋጅ ቁጥር 49/1989 (እንደተሻሻለው) እና በደንብ ቁጥር 47/1991 መሠረት በተሰጠው ሥልጣንና ተግባር መሠረት ወደ አገር ውስጥ ለሚገቡ የቴሌኮሙኒኬሽን መሣሪያዎች የቴክኒክ ብቃት ማረጋገጫ ይሰጣል፡፡ የቴክኒክ ብቃት ማረጋገጫ የሚሰጠው መሣሪያዎቹ ኤጀንሲው ያወጣቸውን ደረጃዎች ማሟላታቸውን በማረጋገጥ ነው፡፡

ኤጀንሲው የሚሊኒየሙን በዓል ለማክበር ወደ አገር የሚመጡ ኢትዮጵያዊያን፣ ትውልደ ኢትዮጵያዊያንና ሌሎች እንግዶች ወደ አገር ውስጥ የሚገቡ የቴሌኮሙኒኬሽን መሣሪያችን በተመለከተ ስላሉት የሬጉላቶሪ ሁኔታዎች በግልፅ እንዲረዱ ለማድረግና መሣሪያዎቹ አገር ውስጥ ከመጡ በኋላም በተቀላጠፈ ሁኔታ እንዲስተናገዱ ለማድረግ ይህን አጭር ማብራሪያ አዘጋጅቷል፡፡

1. የሚከተሉት የቴሌኮሙኒኬሽን መሣሪያዎች ወደ ሀገር ውስጥ ከመግባታቸው በፊት ወይም ከአገሪቱ የቴሌኮሙኒኬሽን አውታር ጋር ከመገናኘታቸው በፊት ከኤጀንሲው የቴክኒክ ብቃት ማረጋገጫ ማግኘት ይኖርባቸዋል፣

    1.1 ባለገመድ የመደበኛ ስልክ ቀፎ
    1.2 ገመድአልባ የመደበኛ ስልክ ቀፎ
    1.3 የሞባይል ስልክ ቀፎ
    1.4 የሳተላይት ሞባይል ስልክ ቀፎ
    1.5 የፋክስ ማሽን
    1.6 የግል ቅርንጫፍ ማዞሪያ
    1.7 ሞደም
    1.8 ራውተር
    1.9 ስዊች
    1.10 የስልክ ቢል መቆጣጠሪያ
    1.11 የተለያዩ ገመድአልባ የኔትዎርክ መሣሪያዎች
    1.12 የመገናኛ ሬዲዮ
    1.13 የሳተላይት ቴሌቪዥን ሥርጭት መቀበያ ብቻ መሣሪያ

---

* *በዚህ ማብራሪያ ውስጥ የተጠቀሱት ሁኔታዎች እስከ ሰኔ 30 ቀን 1999 ያሉትን ሁኔታዎች የሚገልፁ ሲሆኑ ከዚህ ቀን በኋላ ለውጦች መኖራቸውን ለማረጋገጥ የኤጀንሲውን ድረገፅ www.eta.gov.et ይጎብኙ፡፡*

2. ከተራ ቁጥር 1.1 እስከ 1.5 ያሉት የደንበኞች መገልገያ መሣሪያዎች ከዚህ በፊት በኤጀንሲው የቴክኒክ ብቃት ማረጋገጫ የተሰጠባቸው ዓይነት ከሆኑ አስፈላጊውን የጉምሩክ ፎርማሊቲ ብቻ በማሟላት ወደ አገር ውስጥ እንዲገቡ ይደረጋል፡፡ ከዚህ በፊት በኤጀንሲው የቴክኒክ ብቃት ማረጋገጫ የተሰጠባቸው መሣሪያች ዝርዝር ለጉምሩክ ባለስልጣን የተላለፈ ሲሆን ዝርዝሩንም ከኤጀንሲው ድረገፅ http://www.eta.gov.et/standardsandtype.html ማግኘት ይቻላል፡፡

3. ከተራ ቁጥር 1.1 እስከ 1.5 የተዘረዘሩትን መሣሪያዎች በተመለከተ የሚከተሉትን ማሟላት ጠቃሚ ነው:-

3.1 በተራ ቁጥር 1.1 እና 1.2 የተጠቀሱት ባለገመድ እና ገመድ አልባ የመደበኛ ስልክ ቀፎዎች ኢንተርኔትን በመጠቀም የድምፅ መልዕክት ማስተላለፍ የሚያስችሉ መሆን የለባቸውም፡፡ እንደ IPSTAR እና ሌሎች በቀጥታ የኢንተርኔት ፕሮቶኮልን በመጠቀም የድምፅ ግንኙነት (VoIP) ለማድረግ የሚያስችሉ መሣሪያዎችን ይዞ መግባት ክልክል ነው፡፡ ገመድ አልባ የመደበኛ ስልክ ቀፎዎች ከቤት ውጪ ከ 500 ሜትር ርቀት በላይ መሸፈን የሚችሉ መሆን የለባቸውም፡፡

3.2 በተራ ቁጥር 1.3 የተጠቀሱት የሞባይል የስልክ ቀፎዎች በጂ.ኤስ.ኤም 900 MHz እና 1800 MHz የፍሪኩዌንሲ ባንድ ላይ መስራት የሚችሉ መሆን አለባቸው፡፡

3.3 በተራ ቁጥር 1.4 የተጠቀሱትን የሣተላይት ሞባይል ስልክ ቀፎዎች በተመለከተ በአገሪቱ ውስጥ ፈቃድ አውጥተው እየሰሩ ያሉት Iridium እና Thuraya የተባሉ ኩባንያዎች ናቸው፡፡ ስለዚህ የሣተላይት ሞባይል ስልክ ቀፎዎች በ Iridium ወይም በ Thuraya ኔትወርኮች ላይ የሚሰሩ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡

4. ከተራ ቁጥር 1.6 እስከ 1.13 የተጠቀሱት መሣሪያዎችን በተመለከተ የቴክኒክ ብቃት ማረጋገጫ የሚሰጠው እያንዳንዱን መሣሪያ በመመርመር ስለሆነ ከላይ በተራ ቁጥር ሁለት የተገለጸው አይነት የመሣሪያዎች ዝርዝር የለም፡፡ ሆኖም እነዚህን መሣሪያዎች ወደአገር ውስጥ ከማምጣት በፊት የሚከተሉትን መረጃዎች ማወቁ ጠቃሚ ነው:-

4.1 በተራ ቁጥር 1.11 ላይ የተጠቀሱት ገመድ አልባ የኔትወርክ መሣሪያዎች (Wireless Access Devices) በ2.4GHz ስፐሪድ ስፔክትረም ፍሪኩዌንሲ ባንድ የሚጠቀሙ፣ለቤት ውስጥ አገልግሎት ብቻ የሚውሉ እና ከፍተኛ የማሰራጨት ኃይላቸው ከ100mw የማይበልጥ መሆን አለበት፡፡ መሣሪያዎቹን ከግል መጠቀሚያነት ውጪ ለሌሎች ሰዎች ወይም ለንግድ አገልግሎት ማዋል አይቻልም፡፡

በተቻለ መጠን የመሣሪያውን አጠቃቀም፣ እንደ አስፈላጊነቱ የሚጠቀመውን የፍሪኩዌንሲ ባንድ እና ከፍተኛ የማሠራጨት ኃይል (Maximum Transmission Power)፣ የሚሸፍነውን ርቀት እንዲሁም ሌሎች ዝርዝር የቴክኒክ ስፔሲፊኬሽን የሚገልፅ ማኑዋል መያዝ አስፈላጊ ነው፡፡

4.2 በተራ ቁጥር 1.12 ላይ የተጠቀሱት በአጭር ርቀት፣ በመካከለኛ ርቀትና በረጅም ርቀት ላይ የሚሰሩ የመገናኛ ሬዲዮ መሣሪያዎች (HF፣VHF፣UHF እና ሌሎችም) የሚፈቀደው ከመንግስታዊ ተቋማት በተጨማሪ በሀገር ውስጥ ህጋዊ ፈቃድ ላላቸው የግል ድርጅቶች፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እና አማተር ሬዲዮ ኦፐሬተሮች ወዘተ ሲሆን መሣሪያዎቹን ወደ አገር ውስጥ ለማስገባትም በቅድሚያ የማስገቢያና የፍሪኩዌንሲ ፈቃድ ማግኘትን ይጠይቃል፡፡ ስለዚህ እነዚህን መሣሪያዎች ከመግዛት ወይም ከማዘዝ በፊት ማንዋል በማያያዝ ለኤጀንሲው የፈቃድ ማመልከቻ ማቅረብ አስፈላጊ ነው፡፡

4.3 የሳተላይት ቴሌቪዥን ሥርጭት መቀበያ ብቻ መሣሪያ ይዞ ለመግባት ሲፈለግ የመሣሪያው አይነት፣ ሞዴል፣ የሴሪ ቁጥር፣ የዲሹ ዲያሜትር መጠን እና LNB አብሮ ካለም ይኸው ተጠቅሶ መቅረብ ይኖርበታል፡፡

5. የአገልግሎት ክፍያን በሚመለከት

ኤጀንሲው ለሚሰጠው አገልግሎት ክፍያ መፈፀም ያስፈልጋል፡፡ ክፍያው በብዛት ሳይሆን በመሣሪያዎች አይነት እና ሞዴሎች ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ የክፍያ ዝርዝሩ የሚከተለው ነው፡፡

## የአገልግሎት ክፍያዎች

| ተ.ቁ | የቴክኒክ ብቃት ማረጋገጫ የሚያስፈልጋቸው መሣሪያዎች አይነቶች | የክፍያ መጠን* (በብር) |
|---|---|---|
| 1 | መደበኛ የስልክ ቀፎ | 11.00 |
| 2 | የተንቀሳቃሽ (ሞባይል) ስልክ ቀፎ | 28.00 |
| 3 | የፋክስ ማሽን | 35.00 |
| 4 | የግል ቅርንጫፍ ማዞሪያ (PBX) ወይም ኪ. ቴሌፎን | 120.00 |
| 5 | ሞደም | 29.00 |
| 6 | የኢንተርኔት ቴክኖሎጂን መሠረት ያደረጉ የኔትወርክ መሣሪያዎች | 29.00 |
| 7 | የአለቃና ፀሀፊ ስልክ ቀፎ | 17.00 |
| 8 | ለግሎባል ሞባይል የሳተላይት የግል ኮሙኒኬሽን ጂ.ኤም.ፒ.ሲ.ኤስ - GMPCS) ተርሚናል | 29.00 |
| 9 | የቲ.ቪ.አር.ኦ (TVRO) መሣሪያ | 127.00 |
| 10 | የመገናኛ ሬዲዮ | 45.00** |

ማሳሰቢያ - * ኤጀንሲው በመተግበር ላይ ባለው የመሠረታዊ አሰራር ለውጥ ውጤት መሠረት የክፍያ መጠን ለውጥ ሊደረግ ይችላል፡፡ የክፍያ ለውጡም በትራንስፖርት እና መገናኛ ሚኒስቴር ሲፀድቅ ተፈፃሚ የሚሆን ነው፡፡

** ለመገናኛ ሬዲዮ የተጠቀሰው መጠን ለመሣሪያው ምዝገባና ቴክኒክ ብቃት ማረጋገጫ ሲሆን በሚመደበው ፍሪኩዌንሲ እና ባንድ መጠን ተጨማሪ የፍሪኩዌንሲ ክፍያ ይኖራል፡፡